# መመሪያ

የሞንትጎመሪ ካውንቲ የትምህርት ቦርድ
BOARD OF EDUCATION OF
MONTGOMERY COUNTY

**ተመሣሣይ ምንጮች፡-** ACA, BMA, IGK-RA, IGK-RB, ISB-RA, JEE, JEE-RA
**ኃላፊነት ያለው ጽ/ቤት፡-** የአካዴሚ/ትምህርት ዋና ኃላፊ
የት/ቤት ድጋፍና መሻሻል ም/የበላይ ተቆጣጣሪ

## ለስራ ዝግጁነት

A. **ዓላማ**

ለ pre-K-12 በማስተማሪያ ፕሮግራም ላይ የተካተተውን ስለ ሥራ/ሙያ ዝግጁነት ፕሮግራም ራዕይ ለመስጠት እና ለሁሉም ተማሪዎች የቴክኒክ ስልጠና እና የተጨባጩ ዓለም የስራ ተሞክሮዎች ጥብቅ የአካደሚ ኮርስ ስራ ለመስጠት ነው

ከአራት-ዓመት የኮሌጅ ዲግሪ በተጨማሪ በአጭር-ጊዜ ትርጉም ያለው ለሙያ ማስረጃ እሴት የሚሰጥ፣ በ 21[ኛው] ክፍለ ዘመን ኢኮኖሚ ውስጥ ለተለያዩ ሚናዎች ለማዘጋጀት የሚያስፈልጉ ክህሎቶችን ለማግኘት የሚያስችላቸውን እድሎች ለተማሪዎች ለመስጠት

የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የሙያ ዝግጁነት ፕሮግራም ከሁሉም የስቴት እና የፌደራል ተፈላጊ መመዘኛዎች ጋር ለማጣጣም እና ግለሰቦችን ለከፍተኛ የሙያ ውጤታማነት፣ ወቅታዊ ወይም ለወደፊት የኢንዱስትሪ ፍላጎት በሙያ ሥርተው ለመኖር የሚያስችል ክፍያ የሚገኝበት ሙያዊ ዝግጅት እንዲያደርጉ ለመርዳት

B. **ጉዳይ**

ለከፍተኛ ችሎታ እድሎች፣ ትርጉም ያለው ምንዳ ክፍያ የሚያስገኙ በአሁኑ ወቅትም ሆነ በፍላጎት ብቅ የሚሉ የኢንዱስትሪ ዘርፎች ተማሪዎች በህይወት ዘመናቸዉ በሙሉ የትምህርትና ስልጠና አጋጣሚዎችን ለመከታተል ዝግጁ እንዲሆኑ ይጠይቃሉ።

ተማሪዎች ችሎታቸዉን ከዝንባሌዎቻቸው ጋር እንዲያጣጥሙ እድሎችን ለመስጠት፣ በኤለመንተሪ፣ በመካከለኛ እና ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሙያ ዝግጁነት ትምህርት ሰፋፊ ልምዶችን/ተሞክሮዎችን ይሰጣሉ

1. ግብ ማስቀመጥን፣ ጽናትን፣ ንቁ የመሆን፣ የጊዜ አጠቃቀም፣ በትብብር መማርን፣ እና የራስ ውጤታማነትን በመሳሰሉት፣ ከግንዛቤ/እዉቀት ስልቶች እና የመማር ክህሎቶች እና ዘዴዎች ጋር በዋና ዋና ትምህርቶች እውቀታቸውን ያዳብራሉ፣

2. ተማሪዎችን ከዝንባሌዎቻቸው እና ፍላጎቶቻቸው ጋር የሚጣጣም ሙያ ለማዳበር እንዲችሉ ከዘርፈ-ብዙ ሙያዊ ሥራዎች ጋር እንዲተዋወቁ ማድረግ፣

3. በትምህርት ቤት ልምዶቻቸው ላይ ምን እንደሚያስፈልግ እና ምን መጨመር እንዳለበት ስልታዊ እና ፈጠራ የታከለበት አስተሳሰብ እንዲኖራቸው ማደፋፈር፣ እና

4. ለድህረ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና የሚመኙትን/ፍላጎቶቻቸውን ለማሟላት እንዲችሉ ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ እድሎች የሽግግር ስልጠና/ክህሎት/ሙያዎችን መስጠት።

C. አቋም

1. ከፍተኛ ጥራት ያላቸው፣ የሙያ ሥራ እድሎችን ለተማሪዎች የሚፈጥር ትክክለኛ ሙያዊ/በፕሮፌሽን የሥራ እድሎች እና/ወይም ልምድ የሚካበትባቸው እድሎችን ለማሳደግ ተማሪዎች በበርካታ ኢንዱስትሪዎች እውቅና ያላቸው ከድህረ- ሁለተኛ ደረጃ በኋላ ተቋማት የሚሰጡ የሙያ ትምህርት ማስረጃዎችን፣ ሠርተፊኬቶችን፣ እና/ወይም ከሁለተኛ ደረጃ ዲፕሎማ በላይ የሙያ ስልጠና ለሚጠይቁ ብቃት እንዲኖራቸው የሁለት ዓመት ወይም አራት ዓመት ኮሌጅ ዲግሪዎች እንዲኖራቸው ለማገዝ፣ MCPS ለሙያ ዝግጁነት ራእይ እና ስትራቴጂ ያዳብራል።

    a) የሙያዊ ሥራ ስልጠና ተማሪዎች ገና በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ላይ እያሉ ሠርተፊኬቶችን እና የሙያ ፈቃዶችን፣ እና የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ኮሌጅ ክሬዲት ጨምሮ በኢንዱስትሪዎች-እውቅና የሚሰጣቸው የሙያ ትምህርት ማስረጃዎችን ለማግኘት ያስችላቸዋል።

    b) ለሙያ ዝግጁነት ለሥራ ማስረጃ እና/ወይም ለሙያዊ/ፕሮፌሽናል ክህሎት መሸጋገሪያ እንደ የኮሌጅ ዝግጅት ፕሮግራም አካል በመሆን ጥልቅ አካዴሚያዊ መርሐ ግብርን ማጠናቀቅን ያካትታል።

    c) የሙያ ሥራ ዝግጁነት በ 21 ኛው ክፍለ ዘመን የሚገኙ አዳዲስ የሥራ ድርሻዎችን እና ሙያዎችን ፍላጎት ለማሟላት፣ ተማሪዎችን ምንም ማሻሻያ ሳያስፈልግ በሥራ ህይወት ዘመናቸዉ በሙሉ ቀጣይነት ለሚኖረው ትምህርት ዝግጁ እና ብቁ እንዲሆኑ ያደርጋቸዋል።

2. የሙያ ዝግጁነት የሚያካትተው ዘለቄታዊ ትምህርት እና ሙያዊ ውጤታማነት ለማንኛውም የሙያ ነክ ፈር ቀዳጅ ዋና ተወዳዳሪነት ተፈላጊ ማስተማርን ያካትታል።

    a) ከሙዓለህፃናት (preK)-12 እስከ አስራሁለተኛ ክፍል፣ ተማሪዎች እንደአግባብነቱ፣ መሠረታዊ የሆኑ የሙያ ዝግጁነት እውቀቶችን በአጽንኦት ማሰብ፣ ችግርን ለመፍታት የፈጠራ ስልቶችን መጠቀም፣ በቃል ንግግር እና በጽሑፍ ግንኙነት ማድረግ፣ የቡድን ሥራ እና ትብብር፣ የሚጣረሱ አመለካከቶችን በትንታኔ ማየት እና መገምገም፣ ዓለም አቀፋዊ እና የብዝሃነት ባህል ርቱእነት፣ አመራር፣ ጊዜ-በአግባብ መጠቀም፣ ግብ መመስረት፣ ጽናት፣ ራስን የማስተማር ኃላፊነት፣ የሥራ ውጤቶችን ማደርጀት፣ እና የሚያመርቱትን ሥራ ትክክለኛነት መቆጣጠርና ማረጋገጥ የመሳሰሉትን ያዳብራሉ።

    b) ለሙያዊ ሥራ ዝግጁ መሆን አስፈላጊ መሆኑን መገንዘባቸውን ለማረጋገጥ ስለ MCPS የሙያ ናሙናዎች ፈለጎችን፣ በርካታ ሙያዊ እድሎችን፣ እና ኢንዱስትሪዎች እውቅና/ተቀባይነት ያላቸው የሙያ ትምህርት ማስረጃዎች እና ሠርተፊኬቶች በ MCPS ትምህርት ወቅት እና ከዚያም በኋላ ለማግኘት የሚችሉ መሆኑን ለማስገንዘብ ከሙዓለህፃናት (preK)-12 እስከ አስራሁለተኛ ክፍል፣ ተማሪዎች እና ቤተሰቦች ጋር በርካታ ግንኙነቶች ይደረጋሉ።

    c) ከመካከለኛ ደረጃ/ሚድል ስኩል ጀምሮ ተማሪዎች ለሁለተኛ ደረጃ ትምህት የፈጠራ ክህሎትን ማዳበር እና ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ስልጠና እየተዘጋጁ እግረመንገዳቸውን የሙያ ዳሰሳ እና ዝግጅት ማድረግ ስልታዊ አስተሳሰብ እቅድ እና ልምድ እንዲኖራቸው ማበረታታት/ማደፋፈር።

3. የ MCPS ተማሪዎች በሙሉ በርካታ የሙያ ሥራ ዝግጁነት ኮርሶችን እንደ አጠቃላይ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የትምህርት ፕሮግራም አካል ወይም በብቸኝነት ወይም በዋነኝነት የሙያ ሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞችን ለማቅረብ ለሚጠቅም ለልዩ የሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ፕሮግራም ተደራሽነት ይኖራቸዋል።

a) MCPS በመደበኛው የትምህርት ቀን የሚሳተፉ ተማሪዎችን ጨምሮ፣ በድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሚሰጥ ፕሮግራም ለተማሪዎች ተደራሽ የሆነ የመረጃ አደረጃጀት (formats) በየጊዜው ያዘጋጃል ያስፋፋል።

b) MCPS እንደየፕሮግራሞቹ ሁኔታ የተለያየ ተማሪዎች በአካባቢያቸው ት/ቤት የማያገኟቸውን የሙያ ፕሮግራሞች ፈለግ ተደራሽ ለማድረግ በተማሪ ፍላጎቶች፣ አቅም፣ እና የማመልከቻ እና የመግቢያ መስፈርት ላይ የተመሠረቱ የተለዩ እድሎችን ይሰጣል።

c) MCPS የሙያ ዝግጁነት ትምህርት ፕሮግራሞችን በመደኛነት በመገምገም ለዝቅተኛ ውጤት፣ የመግቢያ፣ ወይም ለፕሮግራም ውጤታማ እንዳይሆን ምክንያት የሚሆኑ እንቅፋቶችን የማስወገጃ ስልቶችን ይተገብራል።

4. ለመምህራን፣ ካውንስለሮች፣ እና ለአስተዳዳሪዎች የሚከተሉትን አስመልክቶ ሙያዊ የትምህርት እድሎች ይሰጣቸዋል

a) ከክልላዊ የሥራ ገበያ ጋር ተዛማጅነት ያለው ከፍተኛ የሥራ-ሙያ፣ ጠቃሚ/የመኖሪያ ክፍያ፣ የባለሙያ ፍላጎት ያላቸው የኢንዱስትሪ ዘርፎች እና ሥራዎች፣ ለተማሪዎች ሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ካጠናቀቁ በኋላ ትርጉም ያለው የሙያ ሚና እንዳለ እንዲያውቁ ለማድረግ፣ እና

b) MCPS ለሙያ ሥራ ዝግጁነት እና ተማሪዎች ያሏቸው እድሎች፣ ተማሪዎችን እና ወላጆችን/ሞግዚቶች ለድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ስልጠና ሲዘጋጁ እግረመንገዳቸውን MCPS ሙያን ከሥራ ጋር የማገናኘትን ልምድ ፈጠራ እና ስልታዊ አማራጮችን እድሎችን እንዲያስቡ ያግዛል።

5. ተማሪዎች ኢንዱስትሪዎች የሚፈልጉት አይነት ሙያዊ ዝግጁነት የትምህርት ፕሮግራሞችን በማስተማር ተማሪዎችን የመርዳት አቅም ያላቸው እና የሙያ ትምህርት በመስጠት ቀጥተኛ ተሳትፎ ለሚኖራቸው ሠራተኞች ከወቅቱ ፈጣን የአካደሚክ ደረጃ እና የኢንዱስትሪ ፍላጎት ጋር እንዲራመዱ ድጋፍ ለመስጠት የሚችሉ በከፍተኛ ሙያና ልምድ የተካኑ ችሎታ ያላቸው ሠራተኞችን ለመመልመል MCPS ከፍተኛ ጥረት ያደርጋል።

6. MCPS በሁሉም ደረጃ ከሚገኙ ተማሪዎች፣ እና ለወላጆች/ሞግዚቶች እና ሌሎች ቁልፍ የሆኑ ባለድርሻ አካላትን በመድረስ ስለ - ግንዛቤ ለማስጨበጥ ቀጣይነት ያለው ጥረት ያደርጋል

a) በአካባቢ እና በሪጅን የሙያ ሥራ ግብይት የኤኮኖሚያዊ ለውጦች እና የሙያ ሥራ እድሎች፣

b) ኮሌጅ ለመግባት ከሚደረግ መሰናዶ ጋር በተጓዳኝነት የሙያ ዝግጅት ጠቃሚነት፣ እና

c) የ MCPS ሙያዊ ሥራ ዝግጁነት ፕሮግራሞች እና ከተማሪ ፍላጎት/ዝንባሌ ጋር የተጣጣመ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ አማራጮችን በእውቀት ለመወሰን የሚሰጡ ድጋፎች።

7. እያንዳንዱ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት ለተማሪዎች እና ለቤተሰቦቻቸው ከተማሪ ፍላጎት/ዝንባሌ ጋር የሚጣጣሙ የ MCPS ሙያዊ ዝግጁነት ፕሮግራሞች እና ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርትና ስልጠና ተፈላጊ ነገሮችን በሚመለከት የሙያ አማካሪ ይኖራል።

a) MCPS ተማሪዎች በሙሉ ታሪካዊ መሰናክሎችን ወይም የጅምላ አመለካከቶችን ትተው የራሳቸውን ግቦች እና ፍላጎት/ዝንባሌ ላይ ትኩረት በማድረግ እንዲሠሩ ያበረታታል። የሙያዊ ፈለግ ተደራሽነት እና ተሳትፎ በግላዊ ባህርይ ሁኔታ አይወሰንም/አይተነበይም፣ በሞንትጎመሪ

ካውንቲ የትምህርት ቦርድ ፖሊሲ (ACA) ድንጋጌ መሠረት፣ከአድሎአዊነት የጸዳ፣ ፍትኃዊ፣ እና የዳበረ ባህላዊ ንቃት /Nondiscrimination, Equity, and Cultural Proficiency፡፡ ፐረት-ትጋትን የሚጠይቁ ፕሮግራሞች፣ አተያይ/ትልማቸውን በማዳበር ትርጉም ያለው ሥራ እንዲያከናውኑ በማዘጋጀት ተማሪዎች በርካታ እድሎች ይሰጣቸዋል፡፡

b) በከፍተኛ ትምህርት ወይም በአንዳንድ ሙያዊ ሥራ ዘርፎች በታሪክ አነስተኛ ውክልና ካላቸው ቤተሰቦች እና የማህበረሰብ ተማሪዎች ወደ ተገቢው ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ የመግባት እድላቸውን ለማስፋት በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት መውሰድ ያለባቸውን ተፈላጊ ኮርሶች እና ፈተናዎች የመማር እድሎች ይኖራቸዋል፡፡

8. የ MCPS ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት የሙያ እና የቴክኖሎጂ ትምህርት (CTE) ፕሮግራሞች ከሜሪላንድ ስቴት የሙያ ትምህርት ክለስተር ሥርዓት (MSDE)ጋር የሚጣጣሙ ናቸው፡፡

a) እነዚህ ፕሮግራሞች ለተማሪዎች የሚሰጡት ተማሪዎች ብቃት እንዲኖራቸው የሚያስችሉ ዋና የአካደሚክ ትምህርቶችን ለሙያው ከሚያስፈግሉ ፕሮፌሽን ክህሎት ጋር በእቅድ እና ተከታታይነት ያላቸው ፕሮግራሞችን ነው፡፡

(1) በ CTE ፕሮግራሞች የሚሳተፉ ተማሪዎች የሚማሩት ተያያዥነት ያለው ይዘቱ ጥብቅ የሆነ ለሁሉም ሌሎች ተማሪዎች የሚሰጥ አይነት ደረጃ የጠበቀ ጠንካራ አካደሚክ ኮርስ ነው፡፡

(2) እያንዳንዱ ፕሮግራም ተከታታይነት ያለው ጠቃሚ ኮርሶችን እና የማጠናቀቂያ/ማጣሪያ ልምዶችን እንደ ኢንተርንሽፕ ወይም የኮሌጅ ኮርስ ያካተተ ነው፡፡

(3) MCPS ኢንተርንሽፕ እና ሙያን የሚያሠለጥኑ ሥራን መሠረት ያደረጉ የትምህርት ልምዶችን እንደ ሙያ ሥራ ዝግጁነት ፈለግ አካል በማድረግ ያበረታታል፡፡

(4) አብዛኛዎቹ ፕሮግራሞች የ ኢንዱስትሪ/ፕሮፌሽን ሠርተፊኬት ወደማግኘት ያስችላሉ/ያመራሉ፡፡

b) ስለ ሙያ ትምህርት ክለስተሮች በ MSDE ከተገለጸው ተጨማሪ፣ የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) የኢንዱስትሪ ፍላጎት፣ የተማሪ ዝንባሌ፣ የሠራተኛ፣ እና የፋሲሊቲዎች አቅም በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ፕሮግራሞችን ይሰጣል፡፡

9. የሞንትጎመሪ ካውንቲ ፐብሊክ ስኩልስ (MCPS) ከአካባቢ የሥራ ግብረኃይል ኤጀንሲዎች ተወካዮች እና ከበርካታ የአካባቢ ወይም ሪጅናል ቢዝነስ ወይም ኢንዱስትሪዎች ጋር ቀጣይነት ባለው ሁኔታ ፕሮግራሞችን ለማዳበር እና ለመተግበር ግብአቶችን አስፈላጊ በሆኑበት ሁሉ ስለማቅረብ ምክክር ያደርጋል፡፡

a) ቀልጣፋ/ፈጣን ትብብር በ MCPS አካደሚክ ፕሮግራም፣ እና ጠቃሚ ደረጃ የጠበቁትን በመለየት፣ ካሪኩለም፣ የወቅቱ ቴክኖሎጂ እና መሣሪያዎች፣ እና በኢንዱስትሪ እውቅና ያለው የሙያ ማስረጃዎች፣ እንዲሁም የዋሽንግተን ሜትሮፖሊታን ሪጅን እና የሞንትጎመሪ ካውንቲ አካባቢ የሥራ እድሎች እና የኤኮኖሚ እድገት ፍላጎቶች መካከል ቅንጅትን ያዳብራል፡፡

b) የድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት እና ሥራን መሠረት ያደረጉ የትምህርት እድሎችን ለመለየት እና ለማበረታታት MCPS ከቢዝነስ፣ የመንግስት ኤጀንሲዎች፣ ኮሌጆች እና ዩንቨርስቲዎች፣ እና ከሌሎች የማህበረሰብ ቡድኖች ጋር በአጋርነትና በትብብር ይሠራል፡፡ እነዚህ፣ በዚህ ብቻ ባይወሰኑም፣ የንግድ ምስረታዎችን ያካትታሉ፡፡

**D.** **ተፈላጊው ውጤት**

ሁሉም ተማሪዎች እንደፍላጎታቸው እና እንደየዝንባሌአቸው ለወቅቱ የኢንዱስትሪ ፍላጎት ለከፍተኛ የሙያ ክፍያ ሥራዎች የስልጠና እድሎችን በመጠቀም እና ውጤታማ ለመሆን ወደ ድህረ-ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ለመግባት፣ ብቃት፣ የሙያ ችሎታ፣ እና እውቀት ኖሯቸው ይመረቃሉ።

**E.** **የአተገባበር ስልቶች**

ይህንን ፖሊሲ እንደአስፈላጊነቱ ተግባራዊ ለማድረግ የትምህርት ቤቶች ዋና የበላይ ተቆጣጣሪ የአፈጻጸም ደንቦች/መመሪያዎችን ያዘጋጃል።

**F.** **ግምገማ-ክትትል እና ሪፖርት**

ይህ ደንብ በቦርድ የማሻሻያ መመርያ መሰረት ክለሳ ይደረጋል።

**ተዛማጅ ምንጮች፡-** Every Student Succeeds Act (P.L. 114-95); Strengthening Career and Technical Education for the 21st Century Act (Reauthorization of the Carl D. Perkins Career and Technical Education Improvement Act of 2006) (P.L. 115-224); Maryland College and Career Readiness and College Completion Act of 2013 (SB740, 2013); *Annotated Code of Maryland, Education Article*, *Career and Technology Education Programs*, §21-101 and §21-201-204; *Code of Maryland Regulations* 13A.04.02.01-.06; Montgomery County Board of Education Resolution No 25-04

**የዚህ ፖሊሲ ትርከት፡-** Resolution No. 609-72, October 10, 1972, reformatted in accordance with Resolution 333-86, June 12, 1986, and Resolution No. 458-86, August 12, 1986, accepted by Resolution No. 518-86, September 22, 1986; reformatted March 1998; amended by Resolution No. 251-19, April 9, 2019.